# አንድነት በጊዜ!

ተው ስማኝ አገሬ!

ተው ስማኝ አገሬ!

አንድነት ነው ድሌ፤ አነድነት ነው ክብሬ።(ኢትዮጵያ)

ተባብረው ያሰቡት፤

በህብር የወጠኑት፤

በጋራ ያቀዱት፤

በአንድነት የሠሩት፤

ውሉ ጠንካራ ነው አይበጅም ለጠላት፤

አይፈርስም በጠላት።

ተባበሩ ሲለን፤

አንድ ሁኑ ሲለን፤

አመታት አለፉ ከፋው ህዝባችንን።

ያለፍወ አለፈ፤

ጊዜውም ከነፈ፤

በተስፋ አቅንቶ ሲጠብቅ ህዝባቸህን፤

ሶሰተኛ አይዘን አይለፍ እጣችን።

ተባበር አገሬ፤ ተባበር ህዝባችን፤

በርታ ተበራታ አብስረው ድልህን፤

በህብረት ትመመው ንጠቅ ነጻነትክን።

በውስጥም በውጭም፤

ህዝብ አገር ይታደም፤

ካለድል መመለስ ዛሬ አይታሰብም፤

ቁረጥና አብር ሌላ መንገድ የለም።

ህዝብ እየተጋዘ መከራ ሲጋተው፤

አኗኗሩ መሮት እለቱ ሲከብደው፤

ሲያሰርና ሲፈታ ሲያሳድድ ሲገለው፤

ከቤቱ ካገሩ ፈንቅሎ ሲሰደው፤

ከቀዬው በትኖ ማደሪያ ሲያሳጣው፤

መሟገት መራኮት በሆነ ባልሆነው፤

ለምንስ ይበጃል ማንን ሊጠቅም ነው??????

ጊዜ ጊዜ ላይ ነው፤

ውል ነገሩ ያልው፤

ሲመርጥ ሲመራረጥ መተኪያ ሲፈልግ፤

የህዝባችን ህብረት ምን አለበት ቢያድግ?????

ለስልጣን ከሆነ የሚሾም ህዝብ ነው፤

ሲፈልግ የሚሽር ሊያወጣ ሊያወርደው፤

ሁሉ በጁ ያለው፤ህዝብ ነው ህዝብ ነው፤

ለዝና ከሆነ ስምም ዋጋ የለው፤

ለጥቅም ከሆነ ዘራፊን እየነው፤

ከቶ የት ይደርሳል ሁዋላ ባለዳ ነው፤

የመርህ ከሆነ ሁሉም ለህዝብ ነው፤

ላለፈው ስህተት ታሪክ መሰከረው፤

ተበታትኖ መሮጥ ፋይዳው ምኑ ነው?????

ቶሎ ቶሎ ዛሬ ይህች ቀን አትለፍ፤

ተሰብሰብ ተባበር ላንድነትህ ክነፍ፤

ድል የለም ለብቻ መሮጥ አያዋጣም፤

እድሏ ካለፈች ይመጣል ማልቀስም!!!!!!!

መጠላለፍ ይቅር፤

ለአንድነት አብር፤

ለድል ለነጻነት ላርነት ለክብር፤

አገርን ለማዳን የላላውን ወጥር፤

አስልተህ ተራመድ በቅጥ በውል ቀምር፤

በዛሬ ፈረስ ነው ነገን የምትድር፤

ሌላ አስር አመት ከፊትህ ካይንህ ስር፤

አይተብተብብህ ላንድነትህ ጠንክር፤

ወደ ሁዋላ የለም ወደፊትህ እመር!!!!!

ነገሮች ቢበዙ ባህያ አይጫኑም፤

አቃቂር ቢበዛ መፍትሄ አይሆንም፤

ይበቃል ያለፈው ዛሬ ጊዜ የለም፤

በፍትነት ተራመድ ይጠብቃል ህዝብም።

ተው ስማኝ አገሬ፤

ተው ስማኝ አገሬ፤

አንድነት ነው ድሌ አንድንተ ነው ክብሬ። ኢትዮጵያህ!

ፍአ

07 27 2012